የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 27
ADDIS ABABA 15th May, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፬/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኮቶኑ የተፈረመውን የአካፓ እና የአውሮፓ ህብረት ትብብር ስምምነት ማሻሻያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …. ገጽ ፫ሺ፮፻፭

CONTENTS

**Proclamation No. 524/2007**

Cotonou ACP-EU Partnership Agreement Amendment Ratification Proclamation …. Page 3605

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፬/፲፱፻፺፱

## በኮቶኑ የተፈረመውን የአካፓ አገሮችና የአውሮፓ ህብረት ትብብር ስምምነት ማሻሻያ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በአፍሪካ፣ በካረቢያንና በፓስፊክ ቡድን አባል በሆኑ ሀገሮች በአንድ ወገን እና በአውሮፓ ኮሚኒቲና በኮሚኒቲው አባል አገሮች በሌላ ወገን መካከል ጁን ፳፫ ቀን ፪ሺ በኮቶኑ የተፈረመው የትብብር ስምምነት አንቀጽ ፺፭ ስምምነቱ የሚሻሻልበትን ሥርዓት የሚያቋቁም በመሆኑ፤

በዚህም ሥርዓት መሠረት የስምምነቱ አንቀፆች ማሻሻያ የተደረገባቸው ስለሆነ፤

ይህ ማሻሻያ በሥራ ላይ እንዲውል በየሕገ - መንግሥታቸው በተደነገገው ደንብ እና ሥነ ሥርዓት መሠረት ስምምነቱን በፈረሙ አውሮፓ ህብረት አባል አገሮችና ከአካፓ አገሮች ቢያንስ ሁለትሦስተኛ (፪/፫) በሚሆኑት መፅደቅና የማፅደቂያውም ሠነድ ተቀማጭ መሆን ስላለበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኮቶኑ የተፈረመውን የአካፓ እና የአውሮፓ ህብረት ትብብር ስምምነት ማሻሻያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፬/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 524/2007.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RATIFICATION OF AMENDMENT TO THE ACP-EU PARTNERSHIP AGREEMENT SIGNED IN COTONOU

**WHEREAS,** Article 95 of the Partnership Agreement between the members of the African, Caribbean and Pacific Group of States of the one Part and the European Community and its member states, of the other Part signed in Cotonou on 23 June 2000, establishes the procedure for amending the agreement;

**WHEREAS,** in accordance with this procedure, amendment to the provisions of the agreement has been introduced;

**WHEREAS,** ratification of the amendment in accordance with their constitutional rules and procedures and subsequent deposit of the instrument thereof by member states of the European Union and at least two third of the ACP states which are signatories of this Agreement is a pre-condition to the entry in to force of this amendment;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Cotonou ACP-EU Partnership Agreement Amendment Ratification Proclamation No.524 /2007."

**፪. <u>የማሻሻያውን ስምምነት ስለማፅደቅ</u>**

የአካፓ፣ የካረቢያንና የፓስፊክ ቡድን አባል በሆኑ ሀገሮች በአንድ ወገን እና በአውሮፓ ኮሚኒቲና በኮሚኒቲው አባል አገሮች በሌላ ወገን መካከል ጁን ፳፫ ቀን ፪ሺ በኮቶኑ የተፈረመውን የትብብር ስምምነት የሚያሻሽለው ስምምነት ፀድቋል።

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን ሥራ ላይ እንዲያውል በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification**

The Agreement amending the Partnership Agreement between the members of the African, Caribbean and Pacific Group of States, of the one Part, and the European Community and its member states of the other part, signed in Cotonou on 23 June 2000 is hereby ratified.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is authorized to implement this Agreement in collaboration with appropriate government organs.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**